ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፤
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቍጥር ፲፯/፳፻፱ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**

**በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡**
**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**

**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።**

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እግዝእተብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥ እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥ ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

# ይድረስ፡-

በአባቴ፡ በእግዚአብሔር አብ፥
በእናቴ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤
በሕይወታችን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
ለእኔ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡
የኹለንተና ወንድሞቼና እኅቶቼ ለኾናችሁት፥

በእናቴ ስም በምትጠራው፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ የእናቴ ርስት ጒልት ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት!
እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ህላዌው፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ልጁ ብቻ ሳልኾን፤ የፍጥረቱ ሠሪና ጠባቂ፥ መሪና አስተዳዳሪም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የወንድምነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

## መቅድም

ያለፈውን፡ ፲፮ኛውንና ከዚያ የቀደሙትን፡ ተከታታይ መለኮታውያት ዐዋጆቻችንን፡ በቃሏ ያሰማቻችሁ፡ ቅድስቲቱ እናቴ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም መኾኗን ታውቃላችሁ።

ዛሬ፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ በመለኮትነቴ እና በሰውነቴ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፣ ፈጣሪያችሁና አምላካችሁ፣ ሰላማችሁና መምህራችሁ፣ ካህናችሁና ንጉሣችሁ የኾንሁት፡ **እኔ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነኝ።**

## የዚህ ዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ ምክንያት።

ለዚህ፡ ለአኹኑ የዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ የኾነው ምክንያት፡ ምን እንደኾነ፡ አስቀድሜ ልንገራችሁ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

"እኔ: እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ «'አቡነ ዘበሰማያት! የሰማያት አባታችን ሆይ!' በሚለው እና ደቀ-መዛሙርቴ፡ ጠይቀውኝ፡ ባስተማርኋቸው ጸሎት ውስጥ፡ ‹ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፣ ሀበነ ዮም! የየቀኑን ምግባችንን፡ ዛሬም ስጠን!› በሉ!» ያልሁበትን ምክንያት፡ በትክክልና በእርግጥ ታውቁት ዘንድ፡ አስፈላጊ ከኾነበት፡ ከመጨረሻው የሕይወት ዘመን ላይ ስለደረሳችሁ፡ ይህን እውነታ፡ ዛሬ፡ በዐዋጅ መልክ፡ ይኸው ላሳውቃችሁ፡ ፈቃዴ ኾነ!

## የዐዋጅ ቃሌ፡

በዚህ ረገድ የምላችሁን፡ ይህንኑ ቃሌን፡ እንግዲህ፡ በጽሙና ስሙኝ! ሰምታችሁኝም፡ በሃይማኖታዊ ምግባር ፈጽማችሁት፡ ለጣፋጩ ፍሬያማነቱ አብቁት!

እርሱም፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "እንኳንስ፡ የየዕለቱን ምግባችሁን ቀርቶ፡ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነቴ፡ እንድትኖርዋት እያደረግሁ ያለችውን፡ የቀኗን ሕይወታችሁን እንኳ፡ በህልውናችሁ ልትቀጥሉባት የቻላችሁት፡ በእኔ ነው።"

ይህ ብሂሎቱ፡ "ወበከመ ዐጽቅ፡ ኢይክል ፈርየ ባሕቲቱ፣ እመ ኢሀሎ ውስተ ጕንደ ወይኑ፣ ከማሁ፡ ኢትክሉ ፈርየ፡ ለእመ ኢነበርክሙ ብየ! የወይን ቅርንጫፍ፡ ከግንዱ ከተገነጠለ፣ ብቻውን ሊያፈራ እንደማይችል ኹሉ፡ እናንተም፡ እንዲሁ፡ በእኔ ባትኖሩ፡ በህልውናችሁ ልትቀጥሉና ልታፈሩ አይቻላችሁም።" ከሚለው ቃሌ ጋር እንደሚስማማ፡ እናንተም አምናችሁበት፡ ተቀብላችሁታል። (ዮሐ. ፲፭፥ ፬።)

ምናልባት፡ ከመካከላችሁ፡ አንዳንዶቻችሁ፡ የዚህን እውነታ ትክክለኛነትና እርግጠኛነት፡ እንደልማድ ስለቀጠራችሁት፡ እየራሳችሁ ሳታስተውሉት ቀርታችሁ ይኾናል እንጂ፥ በእየቀኑ እኮ፡ እውን ኾኖ፡ በእየራሳችሁ ሲፈጸም ትመለከቱታላችሁ። ይኸውም፡ <u>በየቀኑ፡ እየሞታችሁ የምትነሡበት ትንግርት</u> ነው። እርሱም፡ እናንተው ራሳችሁ፡ 'የሞት ታናሽ ወንድም!" የምትሉት <u>እንቅልፍ</u> ነው።

አዎን! በዚያን፡ በእንቅልፋችሁ ጊዜ፡ በአጠገባችሁ ማን እንዳለ፣ በእየራሳችሁ ላይና በአካባቢያችሁም፡ ምን እንደሚካኼድ፡ አንዳችም የምታውቁት ነገር፡ ከቶ የለም። ሕይወታችሁን እስከማጣት፡ የሚያደርስ የጥቃት ኹኔታ ሊኖር፥ ሊፈጸምም ይቻላል። ታዲያ! በዚያን ጊዜ፡ የጠበቃችሁና የሚጠብቃችሁ፡ ማን ነው? የፈጠርኋችሁና በሕይወት የማኖራችሁ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር ብቻ ካልኾንሁ በቀር፡ ሌላ፡ ማን ሊኾን ይችላል? አዎን! ሌላ፡ ማንም ሊኾን፡ ከቶ አይቻልም፤ የለምና።

በየአልጋችሁ ላይ፡ ለመኝታ ተጋድማችሁ፡ እንቅልፍ እንዲወስዳችሁ እየተጠባበቃችሁ ሣላችሁ፡ ያ፡ ምሥጢራዊው ረቂቁና መለኮታዊው የጥበብ ሥራዬ የኾነው እንቅልፍ በሚወስዳችሁ ጊዜ፡ ለመኾኑ፡ በእንቅልፍ መወሰዳችሁን እንኳ ታውቁታላችሁን? አታውቁትም እኮ!

እውነታው ይህና እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እየራሳችሁን፡ በፈቃዳችሁና በምርጫችሁ፡ ለሞት አሳልፋችሁ በመስጠታችሁ፡ የሥጋ ሞት ጽዋችሁንም እኮ፡ የምትቀበሉት፡ ልክ፡ እንደዚሁ፡ ይህንኑ፡ በእንቅልፍ መወሰዳችሁን በማታውቁበት ምስጢራዊ ኹኔታ በመኾኑ፡ የሞት ፍርሃት፡ በውስጣችሁ ሊኖር ባልተገባ ነበር! እንግዲያ! ይህን ቀላል የኾነውን፡ የዘወትር እውነታ እንኳ ለማወቅ የተሳናችሁ፡ ደካሞችና አላዋቂዎች በመኾናችሁ አይደለም ወይ፡ "ከዚህ የተነሣ፡ የሞት ፍርሃት ሊኖርባችሁ አይገባም!" የሚለው፡ መንፈሳዊው ኅሊናችሁ፡ በዚሁ ነገር፡ ሳያቋርጥ፡ ከየፊታችሁ እየቆመ፡ ሲፋረዳችሁ የሚኖረው? አዎን፡ ለዚህ ነው።

አኹንም፡ እኔ፡ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር፡ በዚህ ረገድ፡ የምላችሁን ስሙኝ! አዎን! በየዕለቱ፡ በዚያ በእንቅልፍ የሞት መኝታችሁ ሳላችሁ፡ በዚያው፡ ወደዘለዓለሙ የሞት እንቅፋችሁ እንዳትቀጥሉ፡ ጠብቄና በሕይወት አቆይቼ፡ እንደገና ቀስቅሼ የማስነሣችሁ እኔ ነኝ። ይህን እውነታ፡ ታውቃላችሁን? ካወቃችሁ፡ መልካም ኾኖላችኋል። ካላወቃችሁ ግን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ይህችን የእግዚአብሔርን እውነት ዕወቋት!

"እንዲህ፡ በእውነት ስታውቋት፡ አዎን! ጠዋት፡ ከእንቅልፋችሁ በነቃችሁና ከመኝታችሁ በተነሣችሁ ቁጥር፡ እጅግ ደስ ብሏችሁ፡ ሐሤትን ታደርጋላችሁ። አዎን! የዝማሬና የምስጋና ቍርባንንም ታቀርቡ ዘንድ ትተጋላችሁ። በየዕለቱ፡ እየሞታችሁ፤ ከዚያ ሞታችሁም፡ በየዕለቱ፡ እንደገና እየተነሣችሁ ነውና። አዲሲቷንም፡ የሥነ-ፍጥረት ቀን፡ በብርሃናዊው ውበቷ፡ እንደገና እየተቀበላችኋት ነውና።

በዚህ ረገድ፡ አንዱ፡ የእኔ አገልጋይ ነቢይ፦

"አንሰ ሰከብኩ፡ ወኖምኩ፤ ወተንሣእኩ፡ እስመ-እግዚአብሔር አንሥአኒ፤ ኢይፈርህ፡ እምአእላፈ አሕዛብ።

"እኔማ፡ በማታው ጨለማ፡ ተኛሁ፤ እንቅልፍም ወሰደኝ። እግዚአብሔር፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ በእንቅልፍ ሞት ተውጬ ሳለሁ፡ በዚያው እንዳልቀርና ወደዘለዓለማዊው የሞት ዓለም እንዳልሸጋገር፡ በሕይወት ጠብቆና አቆይቶ አስነሥቶኛልና፡ ጠዋት፡ ሕያው ኾኜ እንዳለሁ፡ ነቃሁ፤ ተነሣሁም። ስለዚህ፡ እንኳንስ ከአንዱ የሞት ጽዋዬ ቀርቶ፡ ብዙ ሞትን ሊያደርሱብኝ ከሚመጡብኝ፡ ከአእላፋት የጦር ሠራዊትም አልፈራም። እግዚአብሔር፡ በእየቀኑ፡ እንዲህ ይጠብቀኛልና።" ብሎ የጸለየው፥ ይህም ጸሎቱ፡ እንዲህ ተጽፎ የሚነበበው ለዚህ እኮ ነው። (መዝ. ፫፥ ፭-፮።)

ስለዚህ፡ እንዲህ፡ በየዕለቱ እየሞታችሁ የምትነሡ፤ ከነገም ለመድረሳችሁ፡ ከእኔ በቀር፡ ሌላ ምንም ዓይነት ዋስትና የሌላችሁ ከኾናችሁ፡ ታዲያ! ስለነገ፡ ምን ያስጨንቃችኋል? ከእኔ ከፈጣሪያችሁ፡ የምትፈልጉት አንዳች ነገር ቢኖር እንኳ፡ ለየዕለቱ የሚያስፈልጋችሁን ብቻ መጠየቁ ይበቃችኋል። ምክንያቱም፡ <u>ከእኔ የተሰጣችሁ፡ የመኖሩ ዕድል እና በእኔ ያላችሁ፡ የመኖሩ ዋስትና፡ ለአንዲት ቀን ብቻ ነውና።</u>

ይህንኑም እውነታ፡ ወደዳችሁም፣ ጠላችሁም፡ በየዕለቱ ተገድዳችሁ፡ እየራሳችሁ በምትፈጽሙት፣ ነፍሳችሁና መንፈሳችሁም፡ በዚያው፡ ከሥጋችሁ ተለይተው፡ በሬሳነት ልትቀሩ በምትችሉበት፡ <u>በዘወትሩ የእንቅልፍ ሞታችሁ</u>፡ እውን ኾኖ እየደረሰ፡ ይኸው ትመለከቱታላችሁ።

የዚህ ምስጢራዊ እውነታ፡ **"ኢትትክዙኬ፤ ወኢትበሉ ለጌሠም! እስመ ጌሠምሰ፡ ትሔሊ ለርእሳ፤ የአክላ ለዕለት እከያ፤ ወሥራሓ።**

"ትደርሱባት፥ ወይም፡ አትደርሱባት እንደኾነ፡ ገና የማታውቋት፡ "ነገ"፡ ምናልባት ልትደርሱባት ችላችሁ ከተገኛችሁባት፡ በዚያው፡ በነገዋ ዕለት፡ ታስቡባታለችሁና፡ አኹን ባላችሁባት የዛሬዋ ቀን፡ 'ለነገ!' በማለት፡ ስለነገ አትጨነቁ! የራሷን፡ የቀኒቱን ክፉት፥ ጣርና ጋር መሸከም አቅቷችሁ፥ በአድካሚነቷ እየተሠቃያችሁና እየዛላችሁ ያለችውን፥ አኹን ያላችሁባትን፡ የዛሬዪቱን ቀን፡ እስኪ፡ አስቀድማችሁ፡ በደኅና ማለፉ ይኹንላችሁ!" ከሚለው፡ ከእኔ፡ ከመምህራችሁና ከሰላማችሁ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የምሥራች ቃሌ ጋር የሚጣጣም መኾኑን አስተውሉት። (ማቴ ፮፥ ፴፬።)

**‹ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፣ ሀበነ ዮም!**
**የየቀኑን ምግባችንን፡ ዛሬም ስጠን!› የሚለውን፡ ይህን ጸሎት፡**
**<u>ዛሬም፡ በምውትነት ዓዘቅት፡</u> እየጸለዩት ያሉት፡**
**እነማን ናቸው?**

እዚህ ላይ፡ እንግዴህ፡ በማስተዋል ልታጤኑትና ልትገነዘቡት የሚገባችሁ፡ አንድ ዓቢይ ቍም-ነገር አለ። ይኸውም፡ "<u>‹ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፣ ሀበነ ዮም! የየቀኑን ምግባችንን፡ ዛሬም ስጠን!›</u> በሉ!" ያልኋችሁ፡ ይህ፡ የቀደመው፡ ትምህርታዊ መመሪያዬ የኾነው ጸሎት፡ በእናቴ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ መድኃኒትነትና በእኔ የመስቀል ቤዛ ሰላምነት፡ በመንበረ-እግዚአብሔር-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነታችን ዘንድ፡ ተቀባይነትን አግኝቶና ተፈጽሞ፣ የአዲሱን ኪዳን የትንሣኤ ሕይወትም አኀናጽፎ ያበቃ መኾኑን ባለማወቅ፣ ባለማመንም፡ አኹንም፡ ገና፡ ይህንኑ የቀደመውን ጸሎት እየጸለዩ ያሉ፡ የሰው ወገኖች መኖራቸው ነው። ይህንም እውነታ፡ እናንተም ታውቁታላችሁ።

ታዲያ! እነዚህ ወገኖች፡ እነማን ናቸው? በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን ለይቼ፡ በይፉ እንዳሳውቃችሁ አስፈላጊ ኾኗልና፡ ስሙኝ!

አዎን! እነዚህ የሰው ወገኖች: "ኅድጎሙ ለምውታን: ይቅብሩ ምውታኒሆሙ!

"ሊኖሩበት በሚገባቸው፤ እኔም: በአካለ-ትስብእትና በትንሣኤ አንደበቴ ባስተማርኋቸው፥ ኋላም: እንደተሰፋ ቃሌ: በመንፈስ ቅዱስነቴ: ወደእነርሱ ተመልሼ ባሳሰብኋቸው: በቅዱሱ ኪዳን ሕይወት ሳይኾን: በእንስሳዊው የሥጋ አእምሮአቸው ብቻ እየተንቀሳቀሱና እየተመሩ ያሉትን፤ እየራሳቸውን: በክፉትና በኃጢአት ገድለው: ሙታን ያደረጉትን ሰዎች ተውዋቸው! እንዲህ: እየራሳቸውን ሬሳዎች ያደረጉት: እነዚህ ሙታን: ነፍሳቸውና መንፈሳቸው የተለዩዋቸው በመኾናቸው: ከእነርሱ የባሱ ሬሳዎች የኾኑትን ሙታናቸውን ይቅበሩ!" ለሚለው: ለማይታበለው: ለእኔ: መሲሐዊ ቃሌ: እየራሳቸውን: በፈቃዳቸውና በምርጫቸው የዳረጉት ወገኖች ናቸው።

‹ሲሳየነ: ዘለለዕለትነ፤ ሀበነ ዮም!

የየቀኑን ምግባችንን: ዛሬም ስጠን!› የሚለውን: **ይህን ጸሎት:**

## <u>ዛሬ: በአማናዊ ሕያውነቱ:</u>

## እየጸለዩት ያሉትስ እነማን ናቸው?

በእነዚህ ሙታን ወገኖች አንጻር ደግሞ: ይህንኑ ጸሎት: የሰላሙ ድል ከተገኘበት: ከምሥራቹ ጊዜ አንሥቶ: እስከዛሬ፤ ወደፊትም: ለዘለዓለም: በአማናዊ ሕያውነቱ: እየጸለዩት ያሉትስ እነማን ናቸው? እነዚህንም: ለይቼ: በገሃድ አሳውቃችሁ ዘንድ: አስፈላጊ ከኾነበት: ከመጨረሻው የሕይወት ዘመን ደርሳችኋልና: ስሙኝ!

እነዚህማ: "ወአንተሰ ትልወኒ! ...ወሑር! ወስብክ: መንግሥተ-እግዚአብሔር!

"አንተ ግን ተከተለኝ! ...ኺድናም! ስለእግዚአብሔር መንግሥት ስበክ!" ብዬ: መልስ የሰጠሁትን ደቀ-መዝሙሬን መስለውና ፈለጉን ተከትለው: በቅድስቲቱ የመጀመሪያዋ የመንፈስ ትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ሕይወት የሚኖሩት: ኪዳናውያት እና ኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆቻችን ናቸው። (ማቴ. ፰፥ ፳፩-፳፪። ሉቃ. ፱፥ ፶፯-፳፪።)

አዎን! እኒህ፡ ኪዳናውያን እና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆቻችን፡ ከዛሬ ፩ሺ፱ ዓመታት ወዲህ ጀምረው፡ ይህንኑ፡ "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ! እናንተ ግን ስትጸልዩ፡ እንዲህ በሉ!" ብዬ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለጠየቁኝ ደቀ-መዛሙርቶቼ፡ በትስብእት ሰውነቴ ያስተማርኋቸውን፡ ያንን፡ የቀድሞውን፡ "አቡነ ዘበሰማያት! የሰማያት አባታችን ሆይ!" የሚለውን ጸሎት፣

"በእናቴ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ-መድኀኒትነት እና በእኔው፡ የሰላም መስቀሌ ቤዛነት፡ እኔው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ራሴ ፈጽሜውና ህልው ኾኜ በምገኝበት፡ በእግዚአብሔር ጸባዖት ሥላሴነታችን ተቀብዬው፡ ዘለዓለማዊዉን ፍሬያማ ምላሹን የሰጠኋቸው መኾኔን፡ ዐውቀውትና አምነውበት፣ እንዲህ እያሉ፡ በምስጋና መልክ አዘጋጅተው፡ የሚያቀርቡልን ኾነዋል።

"«ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ፡ አኹን፡ እኛም፡ ስምህን እየጠራን፡ እናመሰግንሃለን።

"«በመዳናችን ምሥዋዕ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በሰላማችን የመስቀል ቤዛ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ስለወረደልን፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም መጣችልን። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ። የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ፡ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት ያዘጋጀህልን መኾንህን፡ በመንፈስ ቅዱስ እንድናውቅ አደረግኸን!» በማለት፣ እኒሁ፡ ኪዳናውያት እና ኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆቻችን፡-

"«አቡነ ዘበሰማያት! ...ወንጼውዐከ፣ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዘ ይብል፡- "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡-

"...ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ምሥዋዐ መድኀኒትነ፡ ዘእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወቤዛ መስቀለ-ሰላምነ፡ ዘእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ። በእንተዝ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ በምድር፣ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ። ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ በምድር። ወመጽአት መንግሥትከ። ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፡ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ። አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ህልዎትነ፤ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ።"

\+ + +

ተዐውደ፡ በግንቦት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ + +